https://t.me/lawethiopia

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መስተዳድር ምክር ቤት

ደንብ ቁጥር 20/1996

10ኛ ዓመት ቁጥር 7
ሀዋሳ ቀን 1996ዓ.ም

በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

የገቢ ግብር ስለማስከፈል በወጣው

አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሕገ-መንግስት አንቀጽ 66 ንዑስ አንቀጽ 6 እና በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 118 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ይህ ደንብ ወጥቷል፡፡

ክፍል 1

ጠ ቅ ላ ላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ " የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መስተዳድር ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 20/1996 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ

1. " አዋጅ " ማለት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 ነው፡፡
2. "የግብር ባለሥልጣን" ማለት በገቢ ግብር አዋጅ 56/1995 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 15 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ገቢዎች ቢሮ እና በተዋረድ በዞን፣ በልዩ ወረዳ እና ወረዳ የሚገኙ የገቢዎች ዴስክ ጽ/ቤት/ እንዲሁም የከተማ አስተዳደር ገቢዎች ዴስክ ጽ/ቤት ናቸው፡፡
3. በዚህ ደንብ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሐረጐች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

ክፍል 2

በሠንጠረዥ (ሀ) መሠረት ስለሚከፈለው ግብር

3. ከግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የሚከፈሉ ክፍያዎች በሠንጠረዥ (ሀ) መሠረት ግብር አይከፈልባቸውም፡፡

ሀ/ ሠራተኛ ሲታመም ቀጣሪው ለሕክምና አገልግሎት የከፈለለት ገንዘብ፣

ለ/ በሥራ ውል መሠረት ለሠራተኛ የሚከፈል የመዘዋወሪያ አበል፣

ሐ/ የአየር ፀባይ አበል፣

መ/ ሠራተኛው ከመደበኛ የሥራ ቦታው ውጪ ሥራውን ለማከናወን ሲንቀሳቀስ የሚከፈለው የመንገጎ ወጪ እና ውሎ አበል፣

ሠ/ ሠራተኛ ወደተመደበበት የሥራ ቦታ ሲሄድ፣ የሥራ ጊዜውን ጨርሶ ሲመለስ ወይም የውጭ አገር ዜጋ በውሉ መሠረት የሚከፈለው የመንገጎ ወጪ፣

ረ/ የመንግሥት የልማት ሥራ ድርጅቶች ወይም የመንግሥት መ/ቤቶች ቦርድ አባል ወይም ፀሐፊ እንዲሁም የክልሉ መንግሥት ወይም የከተማ አስተዳደሮች በሚያቋቁሟቸው የጥናት ቡድኖች አባል ወይም ፀሐፊ በመሆን የሚከፈል አበል፡፡

ሰ/ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ለማከናወን በመኖሪያ ቤት የሚቀጠሩ ሰዎች የሚያገኙት ገቢ፣

ሸ/ ለተሿሚዎች የሚከፈል የቤት ኪራይና የኃላፊነት አበል /ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡/

ቀ/ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 3 (ለ)፣(መ)፣(ሠ) እና (ሸ) የተዘረዘሩትን ክፍያዎች መጠን ተሰጥቶታል፡፡

4. በዓይነት የሚሰጡ ጥቅሞች ስለሚሰሉበት ሁኔታ

በዓይነት የሚሰጡ ጥቅሞች የሚሠሉበት ሁኔታ በክልሉ ገቢዎች ቢሮ አማካኝነት የወቅቱን የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ በሚወጣ መመሪያ ይሆናል፡፡

5. የግብር ክፍያን በገቢ ላይ ስለመደመር

በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈለው ግብር ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ የተቀናሽ ሳይደረግ ቀጣሪው ግብሩን በሙሉ ወይም በከፊል የከፈለ እንደሆነ በዚህ አካኋን የተከፈለው ግብር፣ በሠራተኛው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ ተደምሮ በአንድነት ይታሰባል።

6. የተወሰነ አገልግሎት ለመስጠት በውል የሚሠራ ሰው ስለሚያገኘው ገቢ

የተወሰነ አገልግሎት ለመስጠት በውል የሚሠራ ሰው በሚያገኘው ገቢ ላይ ግብር ስለማስከፈል የገቢዎች ቢሮ መመሪያ ያወጣል።

ክፍል 3

በሠንጠረዥ (ለ) መሠረት ስለሚከፈለው ግብር

7. ግብር የሚከፈልበት ገቢ

በአዋጁ ክፍለ 3 መሠረት በሠንጠረዥ (ለ) ግብር የሚከፈልበት ገቢ የሚታሰበው ከዚህ በታች እንደተገለፀው ይሆናል።

1. ጠቅላላ ገቢ የሚከተሉትን ይጨምራል።
   ሀ/ ተከራዩ ለአከራዩ በጥሬ ገንዘብና በሌላም ዓይነት የሚከፍለው ሂሣብ፣
   ለ/ ተከራዩ በአከራዩ ስምና ስለአከራዩም ሆኖ የሚከፍለው ሂሣብ፣
   ሐ/ ተከራዩ ከአከራዩ ጋራ ባደረገው የኪራይ ውል መሠረት ለመሬቱ ወይም ለቤቱ ማሻሻያ ወይም ማደሻ የሚደረገው ወጪ፣ በዚህ ዓይነት የሚደረገው የመሬት ወይም የቤት ማደሻ ወይም ማሻሻያ ወጪ ተከራዩ ለአከራዩ ከሚከፍለው የቤት ኪራይ ሌላ በተጨማሪ ተከራዩ ወጪ የሚያደርገው ሲሆን፣
2. ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚታሰብበት ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ 16(1) (ሐ) ከተመለከተው በስተቀር ከጠቅላላው ገቢ ላይ ሌላ ማናቸውም ተቀናሽ አይደረግም።

8. አስተቀድሞ ስለሚፈፀም ክፍያ

ግብር ከፋዩ የሂሣብ መዝገብ የሚይዝ ካልሆነ በስተቀር ለአከራዩ ወይም ለተከራይ አከራይ የሚከፈለው የኪራይ ሂሣብ ከአንድ ዓመት ለሚበልጥ ጊዜ ሲሆን፣ ጠቅላላው ከኪራይ የሚገኘው ገቢ ክፍያው የተፈፀመበት የበጀት ዓመት ገቢ ሆኖ ይቆጠራል። ሆኖም

በእንደዚህ ያለው ገቢ ላይ የሚፈለው ግብር የሚሰላው የተገኘው ገቢ በሚሸፍናቸው ዓመታት በትክክል ተደልድሎ ነው፡፡

9. <u>የንግድ ድርጅትን ስለማከራየት</u>

የንግድ ድርጅትን ለንግድ ሥራው ጥቅም ላይ የሚውሉ ዕቃዎችንና መሣሪያዎችን ከቤቱ ጭምር በማከራየት የሚገኘው የኪራይ ገቢ ግብር የሚከፈልበት በሠንጠረዥ "ሐ" መሰረት ይሆናል፡፡

ክፍል 4

<u>በሠንጠረዥ (ሐ) መሠረት ስለሚከፈለው ግብር</u>

10. <u>ተቀናሽ ወጪዎች</u>

በአዋጁ አንቀጽ 20 እንደተደነገገው በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ትክክለኛ ሂሣብ ለማግኘት ከጠቅላላ ገቢ ላይ የሚከተሉት ወጪዎች ይቀነሳሉ፡፡

1. ለንግድ ሥራው ገቢ ለማግኘት በቀጥታ ወጪ የተደረገ ገንዘብ ሲሆን፣ ይህም የንግድ ዕቃውን ለመሠራት፣ ለመግዛት፣ ወደአገር ለማስገባት ለመሸጥ እንዲሁም እነዚህን ለመሳሰሉት ሥራዎች ሁሉ በቀጥታ ወጪ የሚደረግ ገንዘብ፣
2. ከንግድ ሥራው ጋር ለተያየዘ ጠቅላላ ተግባርና ለሥራ ማሰኪጃ የሚደረግ ወጪ፣
3. ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ላለው ጉዳይ የመድን ዋስትና ለማግኘት የሚከፈል አረቦን፣
4. በገቢዎች ቢሮ በሚወጣ መመሪያ ከሚወሰን ገደብ ሳያልፍ የንግዱን ሥራ ለማስተዋወቅ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚደረግ ወጪ፣
5. የንግድ ሥራው ላገኘው አገልግሎት የሚከፈል ኮሚሽን፣ ይህም ወጪ ተቀናሽ የሚደረገው፣
   ሀ/ አገልግሎቱ የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
   ለ/ ለአገልግሎቱ የተከፈለው ኮሚሽን በአንድ ዓይነት ሁኔታ ተመሳሳይ አገልግሎት ለመስጠት በገበያ ውስጥ እየተከፈለ ካለው ዋና ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ ነው፡፡
6. በውጭ አገር የሚገኝ ኩባንያ ቅርንጫፍ፣ ተቀፅላ ድርጅት፣ የንብረት ግንኙነት ያለው ኩባንያ ሆኖ፣ በክልሉ ውስጥ የንግድ ሥራ የሚያካሂድ በውጭ አገር ለሚገኘው ኩባንያ ዋና መሥሪያ ቤት ወይም የንብረት ግንኙነት ላለው ኩባንያ የሚፈፅመው ማናቸውም ክፍያ ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው፡-
   ሀ/ የተባለው ወጪ ለተፈፀመ አገልግሎት በትክክል የተከፈለ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ/ የተሰጠው አገልግሎት ለንግዱ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና አገልግሎቱ በሌሎች ሰዎች ወይም በቅርንጫፉ፣ በተቀፅላው ድርጅት ወይም የጎብረት ግንኙነት ባለው ኩባንያ በራሱ ሊከናወን የማይችል ሲሆን፣ ነው፡፡

7. የግል ድርጆቶች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወይም የሽርክና ማኅበር ሥራ አስኪያጅ ወይም ሥራ አስኪያጆች በደመወዝ እና በሌላም መልክ የሚከፈላቸው ገንዘብ ከተገቢው በላይ መሆኑን የግብር ባለሥልጣኑ ሲረዳ፣ የንግደ ሥራውን ተፈጥሮ መሠረት በማድረግ ለግብር አወሳሰን ሲባል ከአንድ በላይ የሆኑት ሥራ አስኪያጆች ደመወዝ እንዳይቀነስ ለማድረግ ወይም በማናቸውም ተገቢ መስሎ በታየው ሌላ መንገድ ለማሰተካከል ይችላል፡፡

8. ለንግድ ሥራው ባለቤት ወይም ለሽርክና ማኅበር አባላት ልጆች የሚከፈል ደመወዝ ተቀናሽ የሚደረገው ለተመደቡበት ሥራ የሚጠይቀውን ተፈላጊ መመዘኛ የሚያሟሉ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

11. <u>ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 21 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሚከተሉት ከጠቅላላ ገቢ ላይ ተቀናሽ አይደረጉም፡፡

   ሀ/ ለሥራው ባለቤት ወይም ለሽርክና ማኅበር አባላት ወይም ለእነዚህ የትዳር ጓደኞች፣ የሚከፈል ደመወዝ፣ አበል ወይም በግል የሚሰጣቸው ገንዘብ፣

   ለ/ በንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የተዘረዘሩት በግል የሚያወጡት ወጪ፣ ከንግዱ ሥራ ገቢ ላይ የሚወስዱት ማናቸውም ገንዘብ፣

   ሐ/ ከንግዱ ሥራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት በሌለው ምክንያት የደረሰ ማናቸውም ኪሣራ፣

2. ለአዋጁ አንቀጽ 21 (በ) አፈፃፀም “የንግድ ድርጅትን ወክሎ በተለያዩ ቦታዎች ለመገኘት የሚደረግ ወጪ” የሚባለው ለንግድ ሥራው መስፋፋት ለሚረዱ ከንግድ ሥራው ድርጀት ውጪ ላሉ እንግዶች ለሚደረግ ለመስተንግዶ እንዲውል የሚሰጥ አበል ነው፡፡

3. ለአዋጁ አንቀጽ 21(ነ) አፈፃፀም “የመዝናኛ ወጪ” ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለማናቸውም ሌላ ሰው የሚቀርብ መጠጥ፣ ትምባሆ፣ ማረፊያ፣ መደሰቻ ወይም ማናቸውም ዓይነት መስተንግዶ ነው፡፡

12. ተቀናሽ የሚሆን ወለድ

በአዋጁ አንቀጽ 21 (1) (ሠ) የተመለከተው የወለድ መጣኔ ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው፡-

1. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና ከተሰጣቸው የአገር ውስጥ አበዳሪ ድርጅቶች፣
2. ኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ የንግድ ድርጅቶች ብድር ለመስጠት ከተፈቀደላቸው የውጭ ባንኮች የተገኘ ብድር ሲሆን ነው፡፡
3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም፣ ከውጭ ባንኮች ለተገኘ ብድር የተከፈለ ወለድ ተቀናሽ የሚደረገው የሚከተሉት ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡
   ሀ/ አበዳሪው የውጭ አገር ባንክ ማንኛውንም የብድር ገንዘብ ለማናቸውም ሰው ለመስጠት ያቀደ መሆኑን እና ብድሩን ለማን እንደሚሰጥ የሚገልፅ የፅሑፍ ማስታወቂያ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን መስጠት አለበት፡፡
   ለ/ ተበዳሪው ለአበዳሪው ከሚከፍለው ጠቅላላ የወለድ ሂሣብ ላይ 10% (አሥር በመቶ) ቀንሶ የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው የሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

13. ስጦታ ወይም ዕርዳታ ተቀናሽ የሚደረግበት ሁኔታ

1. ለአዋጁ አንቀጽ 21(2) አፈፃፀም ስጦታ ወይም ርዳታ ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ላይ ተቀናሽ የሚደረገው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡
   ሀ/ ዕርዳታ ተቀባዩ በበጎ አድራጎት ድርጅትነት የተመዘገበ፣ በዚሁ ዘርፍ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው አስተዋፅኦ ያበረከተ እና ስለገንዘብ አጠቃቀሙ እና ስለሂሳብ አያያዙ ግልፅነት እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ አሠራር ያለው መሆኑ አግባብ ባለው አካል ሲረጋገጥ፣
   ለ/ የአገርን ነፃነት ለማስጠበቅ፣ ሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋን ወይም ወረርሽኝን ለመከላከል ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት መንግሥት ባቀረበው የዕርዳታ ጥሪ መሠረት የተሰጠ ዕርዳታ፣
   ሐ/ ለንግድ ላልተቋቋሙ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ተቋማት የተሰጠ ዕርዳታ፣
2. ከዚህ በላይ ለተዘረዘሩት ተግባራት የተሰጠ ዕርዳታ ወይም ስጦታ ተቀናሽ የሚደረገው ከግብር ከፋዩ ዓመታዊ ግብር የሚከፈልበት ገቢ 10% ያልበለጠ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

14. ኪሣራን ስለማሸጋገር

በአዋጁ አንቀጽ 28 በተደነገገው መሠረት ኪሣራ ሊሸጋገር የሚችለው ኪሣራ የሚያሳየው የሂሣብ መዝገብ በግብሩ ባለሥልጣን ተቀባይነት ሲያገኝ ይሆናል፡፡

15. ስለእርጅና የሚደረግ ቅናሽ

1. በአዋጁ አንቀጽ 23 መሠረት ስለእርጅና የሚደረገው ቅናሽ የሚፈቀደው ግብር ከፋዩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያሳይ የሂሣብ መዝገብ ሲይዝ ነው፡፡
   ሀ/ ንብረቱ የተገኘበትን (የተገዛበትን) ጊዜ እና ዋጋ የሚያሳይ ሠነድ/
   ለ/ ንብረቱ ከተገዛበት ጊዜ ጀምሮ ስለእርጅና በጠቅላላው ተቀናሽ የተደረገውን ገንዘብ የሚያስረዳ መዝገብ፣
2. ስለእርጅና ቅናሽ እንዲደረግለት የሚጠይቅ ማናቸውም ግብር ከፋይ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 በተጠቀሱት መዛግብት የሰፈረው ሁሉ እውነተኛና ትክክለኛ ለመሆኑ ለግብር ባለሥልጣን በፊርማ የተደገፈ ማረጋገጫ መስጠት አለበት፡፡
3. በሕግ በተፈቀደው መሠረት ካልሆነ በስተቀር የንግድ ሥራ ሀብትን እንደገና በመገመት የተገኘ ተጨማሪ እሴት ለእርጅና ቅናሽ መሠረት አይሆንም፡፡
4. በአዋጁ የተፈቀደውን የእርጅና ቅናሽ ያጠናቀቁ ንብረቶች የተሸጡ እንደሆነ ሽያጭ የተከናወነው ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል ከሆነ በእነዚህ ንብረቶች ላይ የእርጅና ቅናሽ አይታሠብም፡፡

16. ተቀናሽ የሚደረግ የካፒታል ተሳትፎ

1. ለአዋጁ አንቀጽ 27 አፈፃፀም በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ወይም የተመዘገበ የሽርክና ማኅበር በሌላ ኩባንያ ወይም የሽርክና ማኅበር ውስጥ ሥራ ላይ ያዋለው ትርፍ ተቀናሽ የሚደረገው ከእያንዳንዱ የሂሣብ ዓመት ግብር የሚከፈልበት ገቢ 5% ያልበለጠ ሲሆን ብቻ ነው፡፡
2. ግብር ከፋዩ ተቀናሽ በተደረገው ገንዘብ የገዛውን አክሲዮን ወይም ካፒታል መልሶ የሸጠ እንደሆነ ተቀናሽ የተደረገው ወጪ አክሲዮኑ ወይም ካፒታሉ በተሸጠበት ዘመን ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ ተደምሮ ግብር ይከፈልበታል፡፡
3. ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ የአክሲዮን ግዥ ወይም የካፒታል መዋጮ በአዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት ተቀናሽ አይደረግም፡፡

ክፍል 5

ሌሎች ገቢዎች

17. የካፒታል ንብረቶችን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም የሚሠላበት ዘዴ

ለአዋጁ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃፀም ከካፒታል ዋጋ ዕድገት የተገኘው ጥቅም በሚከተለው አኳኋን ይሠላል፡፡

1. ከካፒታል ንብረቶች ዋጋ ዕድገት በሚገኝ ጥቅም ላይ ለሚከፈለው ግብር እንደአግባብነቱ ቤቱ የተሠራበት ወይም የተገዛበት ወይም በአክሲዮኑ ላይ የሠፈረው ዋጋ መነሻ ሆኖ ይቆጠራል፡፡
2. ከዋጋ ዕድገት ተገኝ የሚባለው ጥቅም ቤቱ ከተሠራበት ወይም ከተገዛበት ወይም በአክሲዮኑ ላይ ከሠፈረው ዋጋ በላይ የተገኘው የዋጋ ዕድገት ጥቅም ይሆናል፡፡
3. በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከዋጋ ዕድገት ተገኝ የሚባለው ጥቅም ሲሰላ ንብረቱ ከተሸጠበት ዋጋ ላይ አግባብ ባለው አካል በሚወሰነው መጠን የዋጋ ግሽበት ማሰተካከያ እና ቤትን በሚመለከት ለመሬትና ለሕንፃው የተከፈለው ግብር ተቀናሽ ይደረጋል፡፡
4. ከቤት ዋጋ ዕድገት የሚገኘውን ጥቅም ለማስላት የቤት ሥራ ፈቃድ በተሰጠበት ጊዜ አግባብ ባለው መሥሪያ ቤት የተመዘገበው የቤቱ ዋጋ ቤቱ የተሠራበት ዋጋ ሆኖ ይወሰዳል፡፡
5. ከቤት ዋጋ ዕድገት በሚገኝ ጥቅም ላይ የሚከፈለው ግብር ተፈፃሚ የሚሆነው በማዘጋጃ ቤት ክልል ውስጥ በሚገኝ ቤት ላይ ነው፡፡

18. ከግብር ነፃ ስለመሆን

በአዋጁ አንቀጽ 37(2) በተደነገገው መሠረት መኖሪያ ቤትን በማስተላለፍ የሚገኘው ጥቅም ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው መኖሪያ ቤቱ ከተላለፈበት ቀን በፊት ባለው የሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለመኖሪያነት ያገለገለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

19. ከንብረት ኪራይ የሚገኝ ገቢ

ለአዋጁ አንቀጽ 35 አፈፃፀም ከንብረት ኪራይ የሚገኝ ገቢ ማለት በንግድ ሥራ ላይ በመደበኛነት ያልተሠማራ ሰው የሚንቀሳቀሱ እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን አልፎ አልፎ በማከራየት የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ነው፡፡

ክፍል 6

ገቢን ስለማስታወቅ እና ግብርን ስለመወሰን

20. <u>የግብር ከፋዮች ደረጃ</u>

የደረጃ “ሀ” የደረጃ “ለ” እና የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች እንደሚከተለው ተመድበዋል፡፡

1. ደረጃ «ሀ» ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሰዎችና ድርጅቶች አጣምሮ ይይዛል፡፡
   ሀ/ በኢትዮጵያ ወይም በውጭ አገር ሕግ መሠረት የተቋቋመ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት፣
   ለ/ የዓመቱ ጠቅላላ ገቢው አምስት መቶ ሺህ ብር (ብር 500,000) የሆነ ወይም ከዚህ ብልጫ ያለው ገቢ የሚያገኝ ማናቸውም ሌላ የንግድ ሥራ፣
2. ደረጃ “ለ” በደረጃ “ሀ” አስቀድሞ ካልተመደበ የዓመት ጠቅላላ ገቢው ከአንድ መቶ ሺህ ብር (ብር 100,000) በላይ የሆነ ማናቸውም የንግድ ሥራ፣
3. ደረጃ “ሐ” ከዚህ ላይ በደረጃ “ሀ” እና “ለ” ከተጠቀሱት በስተቀር የግብር ባለሥልጣን የዓመት ጠቅላላ ገቢው እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር (ብር 100,000) ይደርሳል ብሎ የሚገምተው ማናቸውም የንግድ ሥራ፣
4. ከዚህ በላይ የተመለከተውን የዓመት ጠቅላላ ገቢ መጠን በተመለከተ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ከፍ ወይም ዝቅ ሊያደርግ እንደሚችል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መጠኑ ከፍ ወይም ዝቅ ቢል ይህ ለውጥ በክልሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

21. <u>የሂሣብ መዘገብ ስለመያዝ</u>

የደረጃ “ሀ” እና “ለ” ግብር ከፋዮች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሂሣብ መዛግብቶች መያዝ አለባቸው፡፡

1. ደረጃ “ሀ” ግብር ከፋዮች በዓመቱ መጨረሻ ላይ የዓመቱን የዕዳና ሀብት መግለጫ እንዲሁም የትርፍና ኪሣራ መግለጫ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር ለግብር ባለሥልጣን ማቅረብ አለባቸው፡፡
   ሀ/ ያልተጣራው ትርፍ የተሠላበትን የሂሳብ አሠራር ዘዴ የሚያሳይ ሠነድ፣
   ለ/ የሥራ ማስኬጃና የአስተዳደር ወጭን የማያሳይ ሠነድ፣
   ሐ/ ስለእርጅና የተደረገውን ቅናሽ የሚያሳይ ሠነድ፣
   መ/ ከመጠባበቂያ ወጪ የተደረገውን እና የመጠባበቂያውን ሂሣብ የማያሳይ ሠነድ፣

2. ደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች የትርፍና ኪሳራ መግለጫ በዓመቱ መጨረሻ ላይ ለግብር ባለሥልጣን ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት በሚቀርቡ የሂሣብ መዛግብትና ሠነዶች ውስጥ የሚሰፍሩት ሂሣቦች በወጪና ገቢ ሰነዶች መደገፍ አለባቸው፡፡

22. ደረሰኞች

1. የሂሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የተጣለባቸው ግብር ከፋዮች የሚጠቀሙባቸውን ደረሰኞች ከማሳተማቸው በፊት የደረሰኞችን ዓይነት እና ብዛት በግብር ባለሥልጣን ዘንድ ማስመዝገብ አለባቸው፡፡
2. ማናቸውም የኅትመት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት የግብር ከፋዮችን ደረሰኞች ከማተሙ በፊት ለኅትመት የቀረቡት ደረሰኞች ብዛትና ዓይነት በግብር ባለሥልጣን ዘንድ የተመዘገበ መሆኑን ማጋገጥ አለበት፡፡

23. የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች የቁርጥ ግብር አወሳሰን

1. በአዋጁ አንቀጽ 69 ተተደነገገው መሠረት የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ “1” እና “2” መሠረት ግብር ይከፍላሉ፡፡
2. አንድ ግብር ከፋይ ከተለያዩ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎች ገቢ የሚያገኝ እና እነዚህ ገቢዎች ያልተጣመሩ በሚሆንበት ጊዜ የግብር ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ ሠንጠረዥ 2 እና 3 በተመለከተው ውስጥ በየዘርፉ የሠፈረውን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በማጣመር ውጤቱ በሚወድቅበት ቅንፍ መሠረት ግብሩን ይወስናል፡፡
3. የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋይ ተቀባይነት ያለው የሂሣብ መዝገብ ካቀረበ ግብሩን የሚከፍለው በሂሣብ መዝገቡ መሠረት ነው፡፡
4. ግብር ከፋዩ በአዲስ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ በመሠማራቱ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 100,000 በላይ መሆኑን የግብር ባለስልጣኑ ካረጋገጠ ግብሩን በተገኘው መረጃ መሠረት ይወስናል፡፡
5. የገቢዎች ቢሮ ከዚህ ደንብ ጋር የተያያዘውን የቁርጥ ግብር አወሳሰን ስሌት ማሻሻል ይችላል፡፡

24. ገቢን ስለማስታወቅ

1. ማናቸውም የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋይ

   ሀ/ በበጀት ዓመቱ ያገኘውን ጠቅላላ ገቢ፣

ለ/ ከመደበኛ ሥራው በስተቀር ከሌላ ምንጭ ያገኘውን ገቢ፣

ሐ/ ይሠራው የነበረውን መደበኛ የንግደ ሥራውን የለወጠ ከሆነ አዲሱን የንግድ ሥራ ዓይነት

በአዋጁ አንቀጽ 69 (2) በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ለግብር ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡

2. የግብር ባለሥልጣን የደረጃ "ሀ"፣ "ለ" ወይም "ሐ" ግብር ከፋይ የሚያቀርበውን መግለጫ፣ ሌሎች መረጃዎችን እና የአካባቢ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ ግብር ከፋዩ በተከታዩ የግብር ዘመን በደረጃው እንዲቀጥል ወይም ደረጃው እንዲሻሻል ሊወሰን ይችላል፡፡
3. በክልሉ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በወኪል ወይም በወኪሎች አማካኝነት የንግድ ሥራ የሚያከናውን ከሆነ፣ የገቢውን ማስታወቂያ ማቅረብና በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ግብር መክፈል የወኪል ወይም የወኪሎቹ እና በክልሉ ነዋሪ ያልሆነው ሰው የጋራ ኃላፊነት ነው፡፡

25. <u>ገቢን የማስታወቂያ ሥፍራ</u>

1. የገቢ ማስታወቂያ የሚቀርበው ለግብር ባለሥልጣን ይሆናል፡፡
2. ከአንድ በላይ የሆነ የንግድ ሥራ ያለው ግብር ከፋይ ገቢውን ማስታወቅ የሚገባው የንግድ ሥራው ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ባለው የግብር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ይሆናል፡፡
3. ከዚህ በላይ የተደነገገው ቢኖርም በተለየ ሁኔታ እንዲፈፀም በሕግ ካልተወሰነ በስተቀር ማንኛውም የክልል ግብር ከፋይ ከአንድ በላይ በሆኑ ዞኖች፣ ልዩ ወረዳዎች፣ ወረዳዎችና የከተማ አስተዳድሮች ፈቃድ አውጥቶ የንግድ ሥራ የሚያከናውን ከሆነ ገቢውን ማስታወቅ እና መክፈል ያለበት የንግዱን ሥራ ፈቃድ ላወጣበት ዞን፣ ልዩ ወረዳ፣ ወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የግብር ባለሥልጣን ነው፡፡

26. <u>ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ሥርዓት</u>

በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች፣ የመንግሥት መ/ቤቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አገልግሎቶችና ዕቃዎች ለሚያቀርቡ ግብር ከፋዮች ከሚፈፅሙት

ማናቸውም ክፍያ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 54(2) መሠረት ሁለት በመቶ (2%) የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው ያስቀራሉ፡፡

1. በአንድ ጊዜ ግዥ ወይም በአንድ የዕቃ አቅርቦት ውል ከብር 10,000 በላይ ለሆነ የዕቃ አቀርቦት ከሚፈፀም ክፍያ፣
2. ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት አገልግሎቶች በአንድ ጊዜ ግዥ ወይም አንድ የአገልግሎት ውል ከብር 500 (አምስት መቶ ብር) በላይ በሚፈፀም ክፍያ፣
   ሀ/ ለምክር አገልግሎት፣
   ለ/ ለዲዛይን ሥራዎች፣ ለፅሑፎች፣ ለትምህርት ገለፃዎች እና መረጃን ለማሠራጨት ሥራዎች፣
   ሐ/ ለጠበቆች፣ ለሂሣብ ባለሙያዎች፣ ለኦዲተሮች እና ሌሎች ተመሳይ አገልግሎቶችን ለሚሰጡ፣
   መ/ ሽያጭ ለሚያከናውኑ ሠራተኞች፣ የኪነ ጥበብና የሰፖርት ባለሙያዎች፣ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ሻጮችን ጨምሮ ከማንኛውም ደላላ እና ሌሎችም የኮሚሽን ወኪሎች፣
   ሠ/ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ከሚተላለፉ ማሰታወቂያዎች እና የመዝናኛ ዝግጅቶች፣
   ረ/ ለሥራ ተቋራጮች ከሚከፈል የአገልግሎት ዋጋ፣
   ሰ/ ከሳይንስ ግኝቶች እና የፈጠራ ውጤቶች ባለመብትነት፣
   ሸ/ ኮምፒውተሮችን ጨምሮ ከተለያዩ ማሽነሪዎች፣ ሕንፃዎችና ሌሎች ዕቃዎች ኪራይ፣
   ቀ/ ከጥገና አገልግሎት፣
   በ/ ከልብስ ስፌት፣
   ተ/ ከሕትመት፣
   ቸ/ ከመድን ዋስትና
3. በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 ለገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ተቀናሽ የሚደረግባቸውን የሥራ ዘርፎች ዝርዝር ወይም የገንዘብን መጠን ከፍ ወይም ዝቅ ቢያደርግ ይኸው ለውጥ በክልል ተፈፃሚነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮው የሥራ ዘርፎች ዝርዝር እና የገንዘብ መጠን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

4. በአንድ ጊዜ ሊፈፀም የሚገባውን ግዥ ታክሱ ተቀንሶ ቀሪ እንዳይደረግ በማሰብ ከፋፍሎ በተለያየ ሠነድ መፈፀም በአዋጁ በተደነገገው መሠረት በወንጀል የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

27. ግብሩን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የጣለበት ሰው ግዴታ

1. ከዚህ በላይ አንቀጽ 24 ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከሚፈፀም ክፍያ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረግ ያለበት ሰው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡፡
   ሀ/ ግብር ለተቀነሰበት ሰው ተከታታይ ቁጥር ያለው ሕጋዊ ደረሰኝ ይሰጣል፡፡
   ለ/ ክፍያ የተፈፀመለትን የእያንዳንዱን ሰው ስም እና ሥራ አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን (የተሰጠ ከሆነ) በወሩ ውስጥ ለተጠቀሰው ሰው የተከፈለውን ገንዘብ አጠቃላይ ድምር፣ ተቀናሽ የተደረገውን ግብር ልክ፣ ከግብር ባለሥልጣን በሚሰጠው ቅፅ በየወሩ ሞልቶ ያቀርባል፡፡
   ሐ/ በወሩ ውስጥ ከተከፈሉ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ ቀሪ መደረግ የሚገባውን አጠቃላይ ሂሣብ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ከተመለከተው ቅፅ ጋር ለግብሩ ባለሥልጣን ገቢ ያደርጋል፡፡
2. የገቢዎች ቢሮ በፊደል (ለ) የተመለከተውን ቅፅ አዘጋጅቶ ያሠራጫል፡፡

ክፍል 7
ልዩ ልዩ

28. መረጃ ስለመስጠት

መረጃ የሚሰጠው በአዋጁ አንቀጽ 39 በተፈቀደው ዓይነት ብቻ ሆኖ ይህም መረጃ ሊሰጥ የሚችለው መረጃውን የፈለገው ሰው ለግብር ባለሥልጣን የበላይ ኃላፊ ጥያቄ ሲያቀርብ እና የግብር ባለሥልጣን የበላይ ኃላፊ በፅሑፍ ሲፈቅድ፣ ይሆናል፡፡

29. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

የገቢዎች ቢሮ ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚረዱ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል፡፡

30. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ከሐምሌ 1 ቀን 1994 ጀምሮ ይህ ደንብ በሥራ ላይ እስከዋለበት ጊዜ ድረስ በተገኘ ገቢ ወይም በገቢነት በተመዘገበ ገቢን በተመለከተ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 78/1994 ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

31. ደንቡ የሚፀናበት ቀን

ይህ ደንብ ከ_____ ቀን 1995 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዋጣ _____ ቀን 1996 ዓ/ም

ኃይለ ማሪያም ደሣለኝ

የደ/ብ/በ/ሕ/ክ/መንግሥት

ርዕሰ መስተዳድር